በስመ አብ ፥ ወወልድ ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ፮ አምላክ!

መልእክት ለኦርቶዶክሳውያን!

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት ማን ይታደጋት?

ለለፋት 493 ዓመታት ክርስትናን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት የምዕራቡ ዓለም ሚሲዮናውያን፥ ፖለቲከኞቻቸውና ዐረቡ ዓለም በብዙ ደክሟል። በተለያየ ጊዜ (ከግራኝ አህመድ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ) ብዙ ኦርቶዶክሳውያን ቢጨፈጨፉም ክርስትና ግን ጠላቶቻችን ያሰቡትን ያህል ሊጠፋና ሊዳከም አልቻለም።።

ከ 1966 ወዲህ ግን የምዕራቡ ዓለም ጅቦችም ሆኑ የዐረቡ ዓለም ተኩላዎች የጥቃት መልካቸውን ቀይረው ብዙ ጉዳት አድርሰዋል። የምዕራቡ ዓለም ፀረ ኦርቶዶክስ መሪዎች ሴኪውላሪዝም (ዓለማዊነት)፥ ምሥራቃውያን ደግሞ በኮሙኒዝም ስም በሃገራችን የጎሳ ፖለቲካ እንዲፈጠር አድርገዋል። የተፈጠረው የገሳ (ብሔር?) ፖለቲካ ደግሞ አማራንና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ጠላት የፈረጀ ነበርና፥ በዚህ ሰበብ ባለፉት 34 ዓመታት በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሲታረዱ ኖረዋል፤ ሚሊየኖች ደግሞ ተፈናቅለው ሰቆቃን ሲቀበሉ ኑረዋል፤ አሁንም ቀጥለዋል።።

ዐረቡ (አክራሪው) የወሀቢ እንቅስቃሴ ደግሞ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ጠላት የፈረጀና ማጥፋትን እንደ አላማ ይዞ የቆየ ነው።። ለመቶዎች ዓመታት ከውጪ በማሥረግ ክርስትናን ከኢትዮጵያ ማጥፋት ባለመቻሉ፥ ከ 40 ዓመታት በፊት በ 10 ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊም ወጣቶችን ከኢትዮጵያ ምድር በመመልመልና ወደ ውጪ በመውሰድ፥ ጅሃዳዊ ስልጠና እንዲወስዱ አድርገዋል።።

ኢትዮጵያን ለዋናውና የመጨረሻው ጂሃዳዊ ዘመቻ እንድትመች ለማድረግ ባለፉት 4 አሠርት ዓመታት ሲያመቻቹ ቆይተዋል።። በዚህም ምጣኔ ሀብቱን፥ የፖለቲካ፥ ወታደራዊና የደህንነት መዋቅሩን በሥራቸው ለማድረግ የሠሩት ሥራ ፍሬ አፍቶላቸው፥ አሁን ለመጨረሻው ዘመቻቸው እየተዘጋጁ ይገኛል።።

ከሁሉ የከፋው ደግሞ "መንግሥት" ነኝ ብሎ የተቀመጠውና፥ ራሱን "ብልጽግና" ብሎ የሚጠራው አካል፥ በወዲህ "የኦሮሚያ ሪፐብሊክን" ለመመሥረት፥ በወዲያው ደግሞ አስተዳደሩ ፕሮቴስታንታዊ ለማድረግ በጀመረው ዘመቻ "አማራ እና ኦርቶዶክስ" የሚል ታፔላ በለጠፈባቸው ዜጎች ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈጸም ከጀመረ ድፍን 4 ዓመታት ተቆጥረዋል።።

የሰሜኑ ጦርነትም አማራውንና ትግሬውን ከጎዳው ይልቅ ኦርቶዶክሳውያን እርስ በርሳቸው እንዲፋጁ የተደረገበት ነበር።

በዚህ ሁሉ መካከል ግን በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ ይህ ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ እየታረደ ፣ ወጣት ክርስቲያኖች ምንም እንዳልተፈጠረ ቁጭ ብለን እንመለከታለን። በተለይ በአዲስአበባና በክልል ከተሞች (ይልቁንም በአማራ ክልል) የምንኖር ኦርቶዶክሳውያን፣ የወገኖቻችን መታረድ፣ መደፈር፣ መታሠርና መሰደድ (ነገ በኛ ላይ የማይደርስ ይመስል) ትኩረት ያልሰጠነው ነገር ሆኗል።

ትንሽ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቷል የሚባለው ወጣት እንኳን፣ ለጥምቀት ማንጠፍና ፋሽን ልብስ ቤተ ክርስቲያንን ይታደጋት ይመስል፣ በዓመት ለጥቂት ቀናት ብቻ ወደ ቁምነገር ሲመጣ ይታያል።

ሰለዚህ ምን እናድርግ?

1፣ እንደ ሃገር ኢትዮጵያ፣ በተለይም ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የሳልውና አደጋ ላይ እንዳሉ እንወቅ።

2፣ ከሳልውና የሚቀድም ምንም ነገር የለምና ከአክራሪው፣ ከፕሮቴስታንቱ፣ ከፖለቲከኛውና ከዘረኛው ቡድን ራሳችን፣ ሃገራችንና ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ እንዘጋጅ።

3፣ በተበታተነ መንገድ መጓዝ ለጠላት ይመቻልና፣ በአንድ ልብና ዕዝ ሥር ሆነን የምንታገልበትን አሠራር እንከተል።
4፣ እኛን ሊያዘናጉ ከሚችሉ ማናቸውም ነገሮች ራሳችንን እናቅብ።

5፣ በየዕለቱ አጀንዳዎቻችን ቤተ ክርስቲያናችንና ሃገራችን ይሁኑ።

6፣ ችግሩ ያልገባቸውን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ፈጥነን እናንቃቸው።

7፣ ሁሉም ነገር የሚሳካው የእግዚአብሔር ረዳትነት ሲኖር ነውና በጸሎት እንጠይቅ፤ ንስሃም እንግባ!

ይህንን መልእክት ችላ ብንለው፣ በሰማይም ሆነ በምድር ለሚደርስብን ነገር ሁሉ ተጠያቂዎቹ እኛው እንሆናለን!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!